# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ነሐሴ ጳጉሜ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 63
ADDIS ABABA, 10 Th, September, 2024


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፬/፪ሺ፲፮ ዓ.ም

የሕጋዊ ሥነ-ልክ አዋጅ ……ገፅ ፲፯ሺ፭


## CONTENT


Proclamation No.1344/2024

Legal Metrology Proclamation …Page 17005


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፬/፪ሺ፲፮

## PROCLAMATION NO.1344/2024

### የሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

### A PROCLAMATION ISSUED TO PROVIDE FOR LEGAL METROLOGY SYSTEM

ከንግድ ልውውጥ፣ ከጤና፣ ከደህንነት እና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ልኬቶችንና የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ የሰውን እና የእንስሳትን ጥቅም፣ ጤንነትና ደህንነት ማስጠበቅ እንዲሁም የአካባቢ ብክለትን መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has been found necessary to protect and keep the interest, health and safety of society and animals as well as the environment by ensuring the verification of measurements and measuring instruments used in relation to commercial transactions, health, safety and environmental protection;

የታሸጉ ምርቶች ወደ ገበያ ከመግባታቸው በፊት እና ከገቡም በኋላ መግለጫቸውና የተጣራ መጠናቸው ትክክለኛነት የሚረጋገጥበትን የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ሸማቾች ለሚከፍሉት ዋጋ ተመጣጣኝ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

WHEREAS, it has been found necessary to create a system to control the labeling and net quantity of pre-packaged products, before and after entering into the market, thereby enabling the consumers to get the right product and service for the price they pay;

የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት የቁጥጥር ሥራቸውን እንዲያካሂዱ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ፍትሐዊ የንግድ ስርዓትን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከአለም አቀፍ የሕጋዊ ሥነ-ልክ የአሠራር ስርዓት ማዕቀፎች ጋር የተጣጣመ ሕግ ማውጣት የንግድ እንቅፋትን በማስወገድ ቀጣናዊ ትስስርን ለማጎልበት የላቀ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፤

ሀገራችን ከደረሰችበት የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጣጣመ ህግ በማውጣት ግልጽና ተአማኒ የአለካክ ሥርዓት ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፪) (ረ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕጋዊ ሥነ-ልክ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፬/፪ሺ፲፮"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/"ሕጋዊ ስነ-ልክ" ማለት በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ልኬትን፣የልኬት አሀዶችን፣ የመለኪያ

WHEREAS, it has been found necessary to establish fair trade through creating a conducive environment for the executive bodies to conduct their regulatory activities;

WHEREAS, it is essential to make a law compatible with the International Legal Metrology framework in order to avoid trade barriers and strengthen regional integration;

WHEREAS, it has been found necessary to establish a transparent and reliable measurement system by issuing a law compatible with the current economic development of the country;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (2) (f) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Legal Metrology Proclamation No.1344/2024."

### 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/"Legal Metrology" means enforcing statutory and regulatory requirements relating to verification of measurement,measurement

መሣሪያዎችን እና የልኬት ዘዴዎችን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ ሕግን በሚያስፈጽሙ ተቆጣጣሪ አካላት የሚከናወን ተግባር ነው፤

፪/“የኢትዮጵያ ደረጃዎች” ማለት ሥልጣን ባለው አካል የጸደቁ የመለኪያ መሳሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ ብሔራዊ ደረጃዎችን የሚያጠቃልል ነው፤

፫/“መደበኛ መለኪያ” ማለት አንድን የመጠን መወሰኛ እና የዚህኑ ልኬት ልዩነትን ያካተተ የመጠኑን ምንነት የሚያስረዳ ማመሳከሪያ ወይም ኢታሎን ነው፤

፬/“የማመሳከሪያ መለኪያ” ማለት የመቆጣጠሪያ መለኪያዎችን ወይም ሌሎች መለኪያዎችን አንድ ዓይነት መጠን ለማረጋገጥ ወይም ካሊብሬት ለማድረግ እና ለማመሳከር የተሰየመና በብሔራዊ የሥነ-ልክ ላብራቶሪ ውስጥ የተቀመጠ መለኪያ ነው፤

፭/“የመቆጣጠሪያ መለኪያ” ማለት የመለኪያ መሣሪያን፣የልኬት ስርዓትን ወይም የቁስ መለኪያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ለመቆጣጠር በመደበኛነት የሚያገለግል የልኬት ማገናዘቢያ ነው፤

፮/“አክሬዲቴሽን” ማለት የተስማሚነት ምዘና አካላትና የሥራ አመራር ሥርዓት አማካሪዎች አስቀድሞ የተወሰነ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሦስተኛ ወገን በሚካሄድ ግምገማ የሚሰጥ

units, measuring instruments, and measurement methods which are performed by regulatory bodies;

2/“Ethiopian Standards” means the National Standards for Measuring Instruments and Pre-packaged Products declared by the legally authorized body;

3/“Measurement Standard” means realization of the definition of a given quantity with stated quantity value and associated measurement uncertainty, used as a reference or Ethalon”;

4/“Reference Measurement Standard” means measurement standard designated for the calibration of working measurement standards or other measurement standards for quantities of a given kind kept in the laboratory of national metrology;

5/“Working Measurement Standard” means measurement standard that is used routinely to calibrate or verify measuring instruments, measuring systems or material measures;

6/“Accreditation” means third-party attestation related to a conformity assessment bodies and management system consultants, conveying formal demonstration of their competence to carryout specific conformity assessment

ምስክርነት ነው፤

፯/“ካሊብሬሽን” ማለት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ በመለኪያ መሣሪያው በመጀመሪያ ደረጃ የተገለፀው የልኬት መጠን ከነልኬት እርግጠኛ አለመሆን፣ የመለኪያ ሥርዓት ወይም የማመሳከሪያ ስርዓት በመለኪያ ኢታሎኑ ላይ ከተገለፀው እሴት ጋር ያለውን አንድነት ወይም ልዩነት ለማወቅ የሚደረግ ንጽጽር ነው፤

፰/“ልኬት” ማለት አንድን መጠን በተሻለ ሁኔታ የሚገልጹ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ በሙከራ የተገኙ መጠናዊ ገላጮችን የመወሰን ሂደት ነው፤

፱/“የልኬት አሀድ” ማለት በዓለም አቀፍ ስምምነት የተወሰነ እና ተቀባይነት ያገኘ እውነተኛ ቁሳዊ መጠን ሆኖ ከሌሎች ተመሳሳይነት ካላቸው ቁሳዊ መጠኖች ጋር በጥምርታ በማነጻጸር በአሀዝ የሚገለጽበት ነው፤

፲/“አለምአቀፍ የአሀዶች ሥርዓት” ማለት ዓለም አቀፍ የሚዛንና መስፈሪያ ጠቅላላ ጉባኤ የተቀበለውና በሥራ ላይ እንዲውል የተደገፈ የተቀናጀ የአሀዶች ሥርዓት ነው፤

፲፩/“የመለኪያ መሣሪያ” ማለት በማንኛውም የመለኪያ አሃድ ወይም በመለኪያ አሀድ የሂሳብ ስሌት ውስጥ የተገለፀን የአንድ አካላዊ መጠን፣ ክስተት፣ አካላዊ

tasks;

7/“Calibration” means operation that, under specified conditions, in a first step, establishes a relation between the quantity values with measurement uncertainties provided by measurement standards and corresponding indications with associated measurement uncertainties and, in asecond step, uses this information to establish a relation for obtaining a measurement result from an indication;

8/“Measurement” means process of experiment -ally obtaining one or more quantity values that can reasonably be attributed to a quantity;

9/“Measurement Unit” means real scalar quantity, defined and adopted by convention, with which any other quantity of the same kind can be compared to express the ratio of the two quantities as a number;

10/“International Units System” means the coherent system of units adopted and recommended by the General Conference on Weights and Measures;

11/“Measuring Instrument”means any appliance, equipment, instrument, software or apparatus or any combination thereof by means of which a measurement of physical quantity,

ባህሪ ወይም ሌሎች የልኬት መጠኖችን ለመለካት የሚያገለግል ማንኛውም መሣሪያ፣ ሶፍትዌር ወይም የእነዚህ ጥምረት ነው፤

፲፪/“የዓይነት ወይም የንድፍ ምዘና” ማለት የአንድ የመለኪያ መሣሪያ ዓይነት ወይም ንድፍ አግባብ ያላቸውን የተደነገጉ የደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟላ እና ለተፈለገው ዓላማ የሚውል ስለመሆኑ መመዘን ነው፤

፲፫/“የዓይነት ወይም የንድፍ ማፅደቅ” ማለት በአይነት ወይም በንድፍ ምዘና ሪፖርት ላይ በመመርኮዝ የአንድ የመለኪያ መሳሪያ ዓይነት ወይም ንድፍ ለታለመለት ዓላማ አስተማማኝ የመለኪያ ውጤቶችን እንደሚሰጥ በመተማመን ተግባር ላይ እንዲውል መወሰን ነው፤

፲፬/ “ትክክለኛነት ማረጋገጥ” ማለት የአይነት ወይም የንድፍ ማረጋገጥን ሳይጨምር የመለኪያ መሣሪያዎች ወይም የታሸጉ ምርቶች የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ሲሆን፣ፍተሻን፣ ምልክት ማድረግንና የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን ያካትታል፤

፲፭/“የመጀመሪያ የትክክለኛነት ማረጋገጥ” ማለት ቀደም ሲል ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ያልተሰጠበትን የመለኪያ መሣሪያ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው፤

expressed in any measurement unit or a mathematical function of a measurement unit, may be made;

12/“Type or Design Evaluation” means judging if a particular type or design of a measuring instrument complies with the relevant statutory requirements and is suitable for use for a prescribed purpose;

13/“Type or Design Approval” means a decision of legal relevance rendered based on the type or design evaluation report whether the type or design of a measuring instrument is adequate to carry out the functions for which it has been designed and manufactured;

14/“Verification” means the procedure of inspection,other than type or design approval,conducted to ascertain that a measuring instrument or Pre-packaged Product complies with the requirements of Ethiopian Standards and includes affixing a verification mark and issuing of a verification certificate;

15/“Initial Verification” means verification of a measuring instrument which has not been verified previously;

፲፮ /"ቀጣይ የትክክለኛነት ማረጋገጥ" ማለት ከመጀመሪያ የትክክለኛነት ማረጋገጥ ቀጥሎ በየጊዜው የሚደረግ የመለኪያ መሳሪያ የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

16/"Subsequent Verification" means verification of a measuring instrument which is conducted periodically after the initial verification;

፲፯/"የማረጋገጫ ምልክት" ማለት የመለኪያ መሳሪያው ትክክለኛ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ለማመልከት በመጨፍለቅ፣ በመቅረጽ፣ በመቅዳት፣ በመሰየም፣ ቀድሞ የተጫነ የወረቀት ማህተም በመለጠፍ ወይም በሌላ መልክ የተቀረጸ ወይም የታተመ ማረጋገጫ ነው፤

17/"Verification Mark" means a Mark made by impressing, casting, engraving, etching, branding, affixing pre-stressed paper seal or any other process to indicate whether or not a measuring instrument is verified;

፲፰/"ምልክት ማድረግ" ማለት ምልክትን በመለኪያ መሣሪያው ላይ መለጠፍ፣ ማጣበቅ ወይም ማተም ነው፤

18/"Marking" means posting, affixing or stamping of a mark on a measuring instrument;

፲፱/"ማሸግ" ማለት በመለኪያ መሣሪያው ላይ ያልተፈቀደ ለውጥ ወይም ማስተካከያ እንዳይደረግ ወይም አካሎቹ እንዳይጐድሉ ለመከላከልና ተዓማኒነቱን ለማረጋገጥ በመሣሪያው ላይ መለያ ኮድ ባለው ሽቦ፣ ፕሎምብ ወይም ሌሎች ማሸጊያ ዘዴዎች በመጠቀም በመሣሪያው ላይ የሚለጠፍ፣ የሚያያዝ ወይም የሚታሰር ነው፤

19/"Sealing" means posting or affixing a measuring instrument with any wire plumb or other accessories having an identity code in order to protect such measuring instrument against any unauthorized modification, readjustment or removal of parts;

፳/ "የታሸገ ምርት" ማለት ለገበያ ከመቅረቡ በፊት የተጣራ መጠኑ በቅድሚያ የተገለጸና በመያዣ የተቀመጠ ወይም የታሸገ ምርት ሆኖ እሽጉ ካልተከፈተ ወይም የሚታይ ለውጥ ካልተደረገበት በስተቀር በውስጡ የያዘው ምርት መጠን

20/"Pre-packaged Product" means any product that is enclosed in a container or packed in any manner, and for which its quantity has been determined and indicated for the purpose of sale whose quantity cannot be changed without the pre-package being

ወይም ብዛት ሊለወጥ የማይችል ነው፤

opened or doing a perceptible modification;

፳፩/"የተጣራ መጠን" ማለት የታሸገው ምርት ማሸጊያውን ወይም መጠቅለያውን ሳይጨምር ያለው ክብደት፣ ይዘት፣ ብዛት፣ ርዝመት ወይም ስፋት ነው፤

21/"Net Quantity" means the quantity by weight, volume, number, length or area of a product contained in a package, excluding the packaging or wrappers;

፳፪/"መግለጫ" ማለት ስለታሸገው ምርት መረጃ ለመስጠት ሲባል በታሸገው ምርት, በምርቱ መያዣ ወይም ማሸጊያ ላይ የተለጠፈ፣ የተጣበቀ ወይም የሚታይ ማንኛውም ጽሁፍ፣ ህትመት፣ ምልክት ወይም ምስል ነው፤

22/"Label" means any written, marked, stamped, printed or graphic material affixed to, attached to or appearing upon any pre-packaged product for the purpose of giving information with respect to such product;

፳፫/"የግብይት ስፍራ" ማለት፡-

ሀ) አንድ ሰው በራሱ ወይም በተወካዩ ስም ማንኛውንም ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ማምረት ወይም ግብይት የሚያከናውንበት ቤት፣ተሽከርካሪ፣ መርከብ ወይም ተንቀሳቃሽ መሳሪያ፤

ለ) ማንኛውም የመለኪያ መሳሪያ ወይም የታሸገ ምርት የተቀመጠበት መጋዘን፣ የጉምሩክ መግቢያና መውጫ የፍተሻ በር ወይም ሌላ ስፍራን ያካትታል፤

23/ "Premises" includes:-

a) a house, vehicle, vessel or any other mobile device, where any business, industry,production or transaction is carried out by a person, by whatever name called, whether by himself or through an agent;

b) aware house, a customs checkpoint or other place where any measuring instrument or pre-packaged products are stored or exhibited;

፳፬/" ኢንስፔክተር" ማለት የመለኪያ መሣሪያን ወይም የታሸገ ምርትን የተጣራ መጠን እና መግለጫ ትክክለኛነት ከተደነገገው የደረጃ መስፈርት አንጻር ለማረጋገጥ ምርመራ የሚያከናውን እና በሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር የተከናወነ

24/ "Inspector" means any officer deployed by the Ministry or the Relevant Body who carries out inspection to ensure the accuracy of measuring instruments as well as the net quantity and label of pre-packaged products as per the standard and also supervises the

የትክክለኛነት ማረጋገጥ ሥራ የሚቆጣጠር ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል የመደበው ባለሙያ ነው፤

works undertaken by the legal metrology officer;

፳፭/“የሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር” ማለት የመለኪያ መሣሪያን እና የታሸገ ምርትን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፤

25/“Legal Metrology Officer” means any person who is granted a license by the Ministry to verify measuring instruments and pre-packaged products;

፳፮/“ጠጋኝ” ማለት የመለኪያ መሳሪያ የኢትዮጵያ የደረጃ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ለማድረግ የመጠገን፣ የማስተካከል፣ የማደስ፣ የማጽዳት፣ የመቀባት ወይም ሌላ ማንኛውንም ተዛማጅ አገልግሎት እንዲሰጥ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው፤

26/“Repairer" means any person who is granted a license by the Ministry or relevant body to repair, adjust,restore, clean, lubricate, paint or render any other related services to ensure that measuring instruments conform to the requirements of Ethiopian Standards;

፳፯/“ተጠቃሚ” ማለት የመለኪያ መሣሪያዎችን ወይም የታሸጉ ምርቶችን የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚልክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሸጥ፣ ለንግድ ወይም ለሌላ ማንኛውም የሕጋዊ ስነ-ልክ አላማ የሚገለገል ማንኛውም ሰው ነው፤

27/“User” means any person who manufactures, assembles, exports, imports, distributes, sells or uses measuring instruments or pre-packaged products for commercial and any other legal metrology purposes;

፳፰/“ሚኒስቴር” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

28/“Ministry” means the Ministry of Trade and Regional Integration of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፳፱/"ክልል"ማለት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ (፩) መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፴/"አግባብነት ያለው አካል" ማለት እንደነገሩ አግባብነት በሥልጣን ክልሉ ስር የሚወድቁ የመለኪያ መሳሪያን እና የታሸገ ምርትን የሚቆጣጠር ማንኛውም አስፈጻሚ አካል ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው መሥሪያ ቤት ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሕጋዊ ሥነ-ልክ ተግባራትን እንዲያከናውን በሚኒስቴሩ ውክልና የተሰጠው አስፈጻሚ አካል ነው፤

፴፩/ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፪/በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩/ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ፡-

ሀ) ለንግድ ልውውጥ፣ ለሰውና ለእንስሳት ጤናና ደህንነት እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ አገልግሎት በሚውሉ የኢትዮጵያ ደረጃ በወጣላቸው ልኬቶች፣ የመለኪያ መሣሪያዎች እና እነዚህን መሳሪያዎች

29/"Region" means any region referred under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Diredawa City Administrations;

30/"Relevant Body" means any executive body that regulates measuring instruments and prepackaged products falling under its jurisdiction, or any office authorized to administer trade in a region, or any executive body delegated by the Ministry to oversee legal metrology functions in accordance with this Proclamation, as appropriate;

31/ "Person" means any natural or juridical person;

32/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

1/ This Proclamation in Ethiopia shall apply upon:

a) Measurements and measuring instruments subject to Ethiopian standards which are used in commercial transactions, health, safety of humans and animals as well as environmental protection and persons who manufacture, assemble, export, import,

በሚያመርት፤ በሚገጣጥም፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚልክ፣ ወደ ሃገር ውስጥ በሚያስገባ፣ በሚያከፋፍል፣ ለገበያ በሚያቀርብ፣ በሚጠቀም፣ በሚያረጋግጥ፣ በሚጠግን፤ እና

ለ)በማናቸውም የታሸጉ ምርቶች የተጣራ መጠን እና እነዚህን ምርቶች በሚያመርት፣ በሚያሽግ፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚልክ፣ ወደ ሃገር ውስጥ በሚያስገባ፣ በሚያከፋፍል፣ ለገበያ በሚያቀርብ እና በሚያረጋግጥ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ይህ አዋጅ ለወታደራዊና ለብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት በሚውሉ የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ቁጥጥር ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የህጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት

### ፬.የሚኒስቴሩ እና አግባብነት ያለው አካል ስልጣንና ተግባር

፩/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የሀገሪቱን የህጋዊ ስነ-ልክ ስርዓት ይዘረጋል፣ተግባራዊ መሆኑን ይቆጣጠራል፤

ለ) የመለኪያ መሳሪያዎች የኢትዮጵያ ደረጃዎች እንዲዘጋጁ እና እንዲከለሱ ለሚመለከተው አካል ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቁም ለሕዝብ ያሳውቃል፤

distribute, sell, use, verify and repair such measuring instruments; and

b) Net amount of any Pre-packaged products and to any person who manufacture, pack, export, import, distribute,sell and verify such products in Ethiopia.

2/ This Proclamation shall not apply to the regulation of measuring instruments and prepackaged products used for Military and National Security purposes.

## PART TWO

## LEGAL METROLOGY SYSTEM

### 4. Powers and Duties of the Ministry and the Relevant Body

1/ The Ministry shall:

a) Establish the Country's Legal Metrology System and oversee its implementation;

b) Propose the development and revision of Ethiopian Standards of measuring instruments to the appropriate body and notify their implementation to the public when approved;

ሐ) በመለኪያ መሳሪያዎች ላይ የሚተገበሩ የማረጋገጫ ምልክቶች የአጠቃቀም፣ የአስተዳደር እና የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፤

መ) እንዳስፈላጊነቱ የመለኪያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት፣የአይነት እና የንድፍ ብቃት ማረጋገጫ ላቦራቶሪ ያቋቁማል፤

ሠ) የመለኪያ መሣሪያዎችን ዓይነት ወይም ንድፍ ይመረምራል፣ያጸድቃል፣ ይመዘግባል፣ የተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ረ) በሀገር ውስጥ የሚመረቱ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል ወይም እንዲረጋገጡ ያደርጋል፤ ይመዘግባል፣ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ሰ) ለሕጋዊ ኦፊሰርና ጠጋኝ ፈቃድ ይሰጣል፤

ሸ) የፈሳሽ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ቦቴዎች፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች እና ዴፖዎች፣ የተሽጋጋሪ ሚዛኖች እና ሌሎች አገልግሎታቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ያልተወሰነ የመለኪያ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣

c) Establish a system for the use, administration and regulation of verification marks applicable to measuring instruments and oversee its implementation;

d) Establish, as deemed necessary, a laboratory for the purpose of type or design evaluation and verification of measuring instruments;

e) Inspect, approve and register the type or design of measuring instruments and issue a certificate of suitability;

f) Verify or cause to be verified locally manufactured, export or import measuring instruments, register same and issue a certificate of verification for the use thereof;

g) Give license to legal metrology officer and repairer.

h) Verify or cause to be verified road tankers, liquid storage tankers, underground storage tankers, fuel depots and calibration of weighbridges and other measuring instruments whose service is not limited to one region and issue a certificate thereof, and ensure only such verified measuring

እንዲረጋገጡ ያደርጋል፣አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የተረጋገጡ የመለኪያ መሣሪያዎች ብቻ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

instruments are used;

ቀ)በሀገር ውስጥ የሚመረቱ፣ ወደ ውጭ ሃገር የሚላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን እና መግለጫ ትክክለኛነት ያረ ጋግጣል፣እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ ለሽያጭ መቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ የይለፍ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

i) Verify or cause to be verified the net quantity and label of locally produced,exportor import pre-packaged products and issue a certificate of release for sale;

በ) የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን ያላሟሉ የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ፣ለሽያጭ እንዳይቀርቡ፣ ከገበያ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲወገዱ ወይም አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ያደርጋል ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

j) Withhold the import, export, sale or use of measuring instruments and pre-packaged products which do not conform to the requirements of Ethiopian Standards, or order the recall or disposal of same, or cause other appropriate legal action to be taken;

ተ) በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ የተመለከቱትን መመዘኛ መስፈርቶች ለሚያሟላ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር እና ጠጋኝ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

k) Issue a license to a legal metrology officer and a Repairer who meets the criteria specified by a directive issued here under and oversee their activities;

ቸ)በሥልጣን ክልላቸው ስር የሚወድቁ የመለኪያ መሳሪያዎችን እና የታሸጉ ምርቶችን ትክክለኛነት የመቆጣጠር ሥልጣን ያላቸውን አስፈጻሚ አካላት

l) Coordinate executive bodies who verify measuring instruments and pre-packaged products falling under their jurisdiction and oversee their performance;

ያስተባብራል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ኀ)ሕጋዊ ሥነ-ልክን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፣ ሥልጠና ይሰጣል፣ ሀገር አቀፍ የመረጃ ቋት ያደራጃል፤

ነ) የሀገሪቱ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት ከዓለም አቀፍ የሕጋዊ ሥነ-ልክ ድርጅት የሕግ እና የአሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ ጋር እንዲጣጣም ያደርጋል፤

ኘ) ሕጋዊ ሥነ-ልክን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ደረጃ ሀገሪቱን ይወክላል፤ በአለም አቀፍ መድረኮች ይሳተፋል፣ ኃላፊነት ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት ዓለም አቀፍ፣አህጉራዊናየሁለትዮሽ ግንኙነቶችን ያካሂዳል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፤

አ)በቁጥጥር ሂደት ሕገወጥ ወይም ከደረጃ በታች ሆነው የተገኙ የመለኪያ መሳሪያዎችና የታሸጉ ምርቶች ስለሚወገዱበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤

ከ)ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ክፍያዎችን ያስከፍላል፤

ኸ)ከሕጋዊ ስነ-ልክ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

m) Undertake capacity building, give training and organize national database of Legal Metrology;

n) Make the Country's Legal Metrology System consistent with the legal framework of the International Legal Metrology Organization;

o) Participate and represent the Country at the international and regional level in all matters relating to legal metrology, conduct, coordinate and administer the international, regional and bilateral relations with other legal metrology institutes;

p) Issue directives for the disposal of illegal or substandard measuring instruments and pre-packaged products discovered in the process of inspection;

q) Charge fees for services it renders in accordance with the regulation issued by the Council of Ministers;

r) Perform other relevant functions related to legal metrology.

፪/አግባብነት ያለው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በግብይት ውስጥ ያሉ የመለኪያ መሣሪያዎችን መዝግቦ ይይዛል፣ ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፣ እንዲረጋገጡ ያደርጋል፣ የተረጋገጡ የመለኪያ መሣሪያዎች ብቻ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

ለ)በግብይት ውስጥ ያሉ የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን እና መግለጫ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤ ወይም እንዲረጋገጡ ያደርጋል፤

ሐ)የመቆጣጠሪያ መለኪያ መሳሪያዎችን ያደራጃል፣ይይዛል፤ወቅቱን ጠብቆ በየጊዜው ዕውቅና ባለው የካሊብሬሽን ተቋም ካሊብሬት መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

መ)በመለኪያ መሳሪያዎች እና በታሸጉ ምርቶች ላይ የገበያ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሠ) ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያደረገው ጥናት ተመሰርቶ በሚሰጠው ውክልና መሰረት ለሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰሮች እና ጠጋኞች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ) የሕጋዊ ሥነ-ልክ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃውን ለሚኒስቴሩ ያጋራል፤

ሰ) የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን የማያሟሉ የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ

2/The Relevant Body shall have the following powers and duties :

a) Register measuring instruments used in the market and verify or cause to be verified their accuracy, and oversee that only verified measuring instruments are applied;

b) Verify or cause to be verified the net quantity and label of pre-packaged products in the market;

c) Organize and keep working measurement standards and ensure that these standards are calibrated timely and regularly by accredited calibration laboratories;

d) Carry out market surveillance on measuring instruments and pre-packaged products;

e) Gives licenses and controls the legal metrology officers and inspectors based on the delegation given to it by the Ministry based on its regular research;

f) Organize regional legal metrology database and share data to the Ministry;

g) Take administrative measures or cause a legal action to be taken to prevent the use of measuring instruments and pre-

አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል

ሸ)ሕጋዊ ሥነ-ልክን በተመለከተ ከሚኒስቴሩ ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ቀ)ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ክፍያዎችን ያስከፍላል፡፡

፭ የልኬት አሀዶች ሥርዓት

፩/የኢትዮጵያ የመለኪያ አሃዶች እና የመለኪያ አሀዶች ብዜቶች ሥርዓት በዓለም አቀፍ የሜትሪክ ሥርዓት መሰረት ይሆናል፤ ይህንንም ሕዝቡ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

፪/በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የንግድ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን የልኬት አሀዶች ብዜቶች በመጠቀም የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡

፫/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ በምርምር ደረጃ ወጥቶላቸው ጥቅም ላይ የሚውሉ ሀገር በቀል የልኬት አሃዶችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

packaged products which do not conform to Ethiopian Standard requirements;

h) Work in collaboration with the Ministry concerning legal metrology;

i) Charge fees for services it renders in accordance with the relevant law.

5. System of Measurement Units

1/ The measurement units and multiples of measurement units of Ethiopia shall be the metric system based on the International System of Units and they shall be announced to the public.

2/ Any person who is engaged in commercial activities shall sell goods or services using the measurement units and multiples of measurement units specified in sub-article (1) of this Article.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article 1 of this Article, the Ministry may determine indigenous measurement units standardized by research in accordance with a directive issued here under.

፮.<u>የመቆጣጠሪያ መለኪያ መሳሪያዎችን ስለመጠቀም</u>

፩/ ማንኛውም ኢንስፔክተር ወይም የሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር የመለኪያ መሣሪያን ወይም የታሸገ ምርትን የተጣራ መጠን ትክክለኛነት በሚያረጋግጥበት ጊዜ ካሊብሬት የተደረገ የመቆጣጠሪያ መለኪያ መሳሪያን መጠቀም አለበት፡፡

፪/የመቆጣጠሪያ መለኪያ መሣሪያዎች ካልብሬት የሚደረጉበት ጊዜ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፯. <u>የማመሳከሪያ መለኪያ መሳሪያዎች አጠቃቀም</u>

፩/ማንኛውም ተጠቃሚ ወይም ደንበኛ የመቆጣጠሪያ መለኪያ መሳሪያዎችን ተጠራጥሮ ቅሬታ ቢያነሳ የማመሳከሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ውጤት የመጨረሻ የትክክለኛነት መጠን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

፪/ የማመሣከሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት በሦስተኛ ወገን ዕውቅና በተሰጠው የካሊብሬሽን ላቦራቶሪ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ካሊብሬት መደረግ አለበት፡፡

6. <u>Utilization of Working Measurement Standards</u>

1/ Any inspector or legal metrology officer shall use calibrated Working Measurement Standards during verifying measuring instruments or net quantity of pre-Packaged products.

2/ The period for the calibration of working measurement standards shall be determined by a directive issued hereunder.

7. <u>Utilization of Reference Measurement Standards</u>

1/ Where any user or customer raises a complaint with regard to a working measurement standard, the result of reference measurement standard shall be the final reference for the decision of its correctness.

2/ The reference measurement standard shall be calibrated by an accredited calibration laboratory at least once a year.

## ክፍል ሦስት

## የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ምዝገባ፣ አያያዝ፣ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና ምርመራ

### ፰.የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ምዝገባ

፩/የመለኪያ መሣሪያዎች እና የታሸጉ ምርቶች ምዝገባ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የመለኪያ መሳሪያ የዓይነት ወይም የንድፍ ተስማሚነት ማረጋገጫ፣ የትክክለኛነት ማረጋገጫ እና የታሸጉ ምርቶች የይለፍ ማረጋገጫ በሚኒስቴሩ ሥርዓት ምዝገባ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

፪/ማንኛውም ተጠቃሚ ያመረተውን፣ የገጣጠመውን፣ ወደ ውጭ ሀገር የላከውን፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን፣ ያከፋፈለውን ወይም ለሌላ ያስተላለፈውን የመለኪያ መሳሪያ ወይም የታሸገ ምርት መረጃ መዝግቦ መያዝ እና በመመሪያ ለሚወሰነው ጊዜ ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

፫/ማንኛውም ተጠቃሚ የመለኪያ መሳሪያዎች ወይም የታሸጉ ምርቶች ትክክለኛነት በሚረጋገጥበት ወይም ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜ በዚህ

## PART THREE

## REGISTRATION, HANDLING, VERIFICATION AND INSPECTION OF MEASURING INSTRUMENTS AND PRE-PACKAGED PRODUCTS

### 8. Registration of Measuring Instruments and Pre-Packaged Products

1/ The type or design suitability and verification of measuring instruments as well as the release of pre-packaged products shall be kept in the registry system of the Ministry.

2/ Any user shall record the data of measuring instruments or pre-packaged products that he manufactured, assembled, exported, imported, distributed or sold and keep such register for the period specified by a directive.

3/ Any user shall make available to the inspector or the legal metrology officer the register maintained under sub-article (2) of this Article at the time of verification and inspection of measuring instruments and

አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የያዛቸውን መዝገቦች ለኢንስፔክተር ወይም ለሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር ማቅረብ አለበት፡፡

pre-packaged products.

፬/በመመሪያ የሚወሰኑ የመለኪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማንኛውም ተጠቃሚ እነዚህን መሳሪያዎች ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ማስመዝገብ አለበት፡፡

4/ Any user who sells goods or services using the type of measuring instruments specified by a directive shall enter such measuring instruments in the registry of the Ministry or the Relevant body.

፱. <u>የመለኪያ መሳሪያዎች አያያዝ</u>

፩/ የመለኪያ መሳሪያዎች አያያዝ ለንግድ ዓላማ የሚያገለግል የመለኪያ መሣሪያ ንባብ ለሻጭ እና ለገዥ በግልጽ መታየት አለበት፡፡

፪/የመለኪያ መሣሪያ በማንኛውም ሰው በቀላሉ ልኬቱን ወይም የመለኪያ ውጤቱን ሊያዛባ ለሚችል የማጭበርበር ድርጊት በማይጋለጥበት ሁኔታ መጠበቅ አለበት፡፡

፫/በማንኛውም የመለኪያ መሣሪያ ላይ የሚለጠፉ መግለጫዎች እና የአጠቃቀም መመሪያዎች በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ወይም ቢያንስ ከሁለቱ በአንዱ የተጻፉ መሆን አለባቸው፡፡

9. <u>Handling of Measuring Instruments</u>

1/ The reading display of a measuring instruments used for commercial purpose shall be clearly shown to the seller and the buyer.

2/ Any measuring instrument shall be kept in a manner that is not easily tampered with by any person or fraudulent action that will distort its measurement result.

3/ User manuals and label affixed on measuring instruments shall be written in Amharic and English languages or at least in one of them.

## ፲.የመለኪያ መሣሪያዎችን ዓይነት ወይም ንድፍ ስለ ማጽደቅ

፩/ማንኛውም ተጠቃሚ የዓይነት ወይም የንድፍ ተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው ማንኛውንም የመለኪያ መሳሪያ ወይም የመሳሪያውን ክፍል ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም፡፡

፪/ማንኛውም ተጠቃሚ የመለኪያ መሣሪያ ወይም የመሳሪያውን ክፍል ከማምረቱ፣ ከመገጣጠሙ፣ ወደ ውጭ ሀገር ከመላኩ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባቱ ወይም ለሽያጭ ከማቅረቡ በፊት ዓይነቱ ወይም ንድፉ እንዲጸድቅለት እና የተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሙሉ ዝርዝር የያዘ ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የቀረበው የመለኪያ መሣሪያ ወይም የመሳሪያው ክፍል አይነት ወይም ንድፍ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ሚኒስቴሩ ምርመራ ያካሂዳል ወይም የምርመራ ሥራው

## 10. Type or Design Approval of Measuring Instruments

1/ No user shall manufacture, assemble, export, import or sell any measuring instrument without a certificate of suitability relating to the type or design of such measuring instrument or part thereof.

2/ Any user shall submit to the Ministry a written application, requesting a certificate of type or design approval, giving full particulars of the pattern of the measuring instrument or part there of before manufacturing, assembling, exporting, importing or selling such measuring instrument or parts thereof.

3/ The Ministry shall conduct testing, or it may subcontract such testing to an accredited body to ascertain that the type or design of the measuring instrument submitted under sub-article (2) of this Article complies with the requirements of Ethiopian Standards.

ዕውቅና ባለው ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ማንኛውም የመለኪያ መሳሪያ ወይም የመለኪያ መሳሪያ ክፍል አይነቱ ወይም ንድፉ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ባለው ሦስተኛ ወገን ተረጋግጦ የጸደቀ ከሆነ የተሰጠው የተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

፭/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ወይም (፬) መሰረት የመለኪያ መሳሪያው የደረጃ መስፈርቶችን ካሟላ ሚኒስቴሩ አይነቱ ወይም ንድፉ የጸደቀ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ምልክት በላዩ ላይ ያደርግበታል፣ ለተጠቃሚውም የተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፮/የመለኪያ መሳሪያው የደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚሰጠውን የዓይነት ወይም የንድፍ ማጽደቅ እና የተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መከልከል ይኖርበታል፡፡

፯/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚሰጠው የዓይነት ወይም የንድፍ ተስማሚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት

4/ A certificate of suitability for the type or design of a measuring instrument or part thereof imported to the country shall be acceptable if it is approved by internationally recognized third party.

5/ The Ministry shall issue to the user a certificate of suitability for the type or design approval, and affix an approval mark on it if the measuring instrument passed the undergone suitability test and complies with the requirements of standards under sub-article (3) or (4) of this Article.

6/ The Ministry shall refuse to issue a certificate of suitability for the type or design approval under sub-article (5) of this Article if the measuring instrument does not comply with the requirements of standards.

7/ The validity period of a certificate of suitability for the type or design approval granted in accordance with sub-article (5) of this Article shall be determined by a directive issued here under.

ጊዜ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፩. የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

፩/ማንኛውም ተጠቃሚ በዚህ አንቀጽ መሠረት የመለኪያ መሳሪያን ለመጀመሪያ እና ለቀጣይ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ለኢንስፔክተር ወይም ለሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም ሲባል ቀጣይ የትክክለኛነት ማረጋገጥ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) የግዴታ ወቅታዊ የትክክለኛነት ማረጋገጥን፤

ለ)ከጥገና በኋላ የሚደረግ የትክክለኛነት ማረጋገጥን፤

ሐ) በተጠቃሚው ጥያቄ መሰረት የሚደረግ የትክክለኛነት ማረጋገጥን፤ እና

መ) በቁጥጥር ወቅት የሚደረግ የትክክለኛነት ማረጋገጥን፡፡

፫/ማንኛውም የመለኪያ መሳሪያ መረጋገጥ ያለበት ለአገልግሎት በሚውልበት ቦታ ከተተከለ ወይም ከተቀመጠ በኋላ ነው፡፡

፬/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የመለኪያ መሳሪያ በተመረተበት ቦታ፣ በጉምሩክ መግቢያና መውጫ በር ላይ ወይም በላቦራቶሪ

## 11. Verification of Measuring Instruments

1/ Any user shall submit measuring instruments for initial and subsequent verifications to the inspector or the legal metrology officer in accordance with this Article.

2/ For the purpose of sub-article (1) of this Article, subsequent verification includes:

a) mandatory periodic verification;

b) verification after repair;

c) Verification by the request of the user; and

d) Verification during inspection.

3/ Any measuring instrument shall be required to be verified only at the place where it has been installed or used.

4/Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, a measuring instrument can be verified at the place of manufacture or a customs checkpoint.

ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

፭/ማንኛውም የመለኪያ መሣሪያ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ተፈትቶ ከተገጠመ ወይም ከተጠገነ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ትክክለኛነቱ እንደገና መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፮/የመለኪያ መሳሪያን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ተግባር የሚከናወነው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል ወይም በህጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር ብቻ ነው፡፡

፯/ሚኒስቴሩ፣ አግባብነት ያለው አካል ወይም የሕጋዊ ስነ-ልክ ኦፊሰሩ የመለኪያ መሳሪያው የኢትዮጵያ የደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው በላዩ ላይ የማረጋገጫ ምልክት ያደርግበታል፤ ለተጠቃሚውም የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፰/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) መሠረት የሚደረግ የመለኪያ መሣሪያ ወቅታዊ የግዴታ የትክክለኛነት ማረጋገጥ ጊዜ እና ሥነ-ሥርዓት በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፪.<u>የመለኪያ መሣሪያዎች ምርመራ ስለማድረግ</u>

፩/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በተጠቃሚው የግብይት ስፍራ በመግባት መደበኛ፣ ድንገተኛ ወይም የቀረበ ቅሬታን መሠረት በማድረግ

5/ If a measuring instrument is dismantled and re-installed or repaired after verification, it shall be duly re-verified before being put into use

6/ Verification of measuring instruments shall be carried out only by the Ministry, the Relevant Body or the Legal Metrology Officer.

7/ The Ministry, the Relevant Body or the Legal Metrology Officer shall affix a verification mark on the measuring instrument and issue a verification certificate to the User if such measuring instrument complies with the requirements of Ethiopian standards.

8/ The period and procedure of mandatory subsequent verification of measuring instruments to be carried out pursuant to sub-article (2) (a) of this Article shall be determined by directive issued here under.

12.<u>Inspection of Measuring Instruments</u>

1/ The Ministry or the Relevant Body may undertake regular, surprise or complaint based visit at the premises of the user for the purpose of inspecting measuring

የመለኪያ መሳሪያ ምርመራ ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ማንኛውም ተጠቃሚ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል ሲጠየቅ የመለኪያ መሳሪያን የማስመርመር ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ምርመራ የሚያደርገው የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ነው፡-

ሀ) የመለኪያ መሳሪያው ዓይነት ወይም ንድፍ የጸደቀ እና የተስማሚነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን፤

ለ)የመለኪያ መሳሪያው ወቅቱን ጠብቆ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሆኑን፤

ሐ)የማረጋገጫ ምልክቱ ወይም የምስክር ወረቀቱ ትክክለኛ መሆኑን፤

መ)ከተረጋገጠ በኋላ በመለኪያ መሣሪያው ላይ ለውጥ አለመደረጉን፤

ሠ) ቀደም ሲል የማረጋገጫ ምልክት የተደረገበት የመለኪያ መሣሪያ በጥቅም ላይ መቆየት የሚችል መሆኑን ወይም ጥገና፣ማስተካከያ ወይም መተካት የሚያስፈልገው መሆኑን፤

ረ)የተደረጉ ምልክቶች ያልተበላሹና በአግባቡ የተያዙ መሆኑን፤

ሰ) የልኬት ውጤቱ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ከተፈቀደው ከፍተኛ የግድፈት መጠን ውጪ አለመሆኑን፡፡

instruments.

2/ Any User shall make measuring instruments available for inspection when requested by the Ministry or the Relevant Body.

3/ The Ministry or the Relevant Body shall conduct inspection of measuring instruments in order to ascertain the following particulars:-

a) The type or design of the measuring instrument is approved and a certificate of suitability is granted;

b) The measuring instrument is timely verified and appropriately calibrated;

c) The verification mark or certificate is valid;

d) No obvious modification is made on the measuring instrument after verification;

e)Any previously verified measuring instrument can be maintained in use or it needs repair, adjustment or replacement;

f) no marks are damaged;

g)The measurement result does not exceed the maximum permissible errors stated in the requirements of Ethiopian

፬/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ፡-

ሀ) የመለኪያ መሳሪያው መመርመሩን ለማሳየት እንደ አግባቡ የንድፍ ወይም የዓይነት ተስማሚነት ማረጋገጫ ወይም የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት መጠቀም አለበት፡፡

ለ)የመለኪያ መሣሪያው ያልተረጋገጠ ከሆነ እና የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው በእያንዳንዱ የመለኪያ መሣሪያ ላይ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት ማድረግ እና የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

ሐ)የመለኪያ መሣሪያው የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ ሆኖ ካገኘው አገልግሎት እንዳይሰጥ ማገድ አለበት፡፡

፭/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም ተጠቃሚው የመለኪያ መሣሪያውን አስተካክሎ ድጋሚ እንዲረጋገጥለት ማድረግ ይችላል፡፡

፮/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ህገ-ወጥ፣ ካልብሬት ያልተደረገ ወይም

standards.

4/ When the Ministry or the Relevant Body conducts inspection under this Article, it shall:

a) Use the verification mark, design or type approval mark, as required, to indicate that the measuring instrument has been inspected.

b) Affix a verification mark and issue a Verification Certificate to the measuring instrument if it is not previously verified and it conforms to the requirements of Ethiopian Standards.

c) Suspend it not to provide service when it is ascertained that the measuring instrument does not comply with the requirements of Ethiopian Standards.

5/Notwithstanding the provisions of sub-article (4) (c) of this Article, the user may rectify the defects of the measuring instrument and make it to be re-verified.

6/ When the Ministry or the Relevant Body finds illegal, un callebrated or non-

የኢትዮጵያ የደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ የመለኪያ መሳሪያ ካገኘ እንዳይሸጥ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

፯/በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚካሄደው የምርመራ ሥራ አፈጻጸም ሲባል በማንኛውም ተጠቃሚ የግብይት ሥፍራ የተገኘ የመለኪያ መሳሪያ ለታለመለት አገልግሎት እንደዋለ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

## ፲፫.የታሸጉ ምርቶችን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ እና ስለምርመራ

፩/ማንኛውም ተጠቃሚ የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን ሳይገልጽ፣ በማሸጊያው ላይ ተገቢውን መግለጫ ሳያደርግ እና ከሚኒስቴሩ የይለፍ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው እነዚህን ምርቶች ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል አይችልም፡፡

፪/ማንኛውም ተጠቃሚ በታሸጉ ምርቶች ላይ የሚያደርገው መግለጫ በቀላሉ የማይላቀቅ፣ የማይፋቅና ለሸማቹ በጉልሕ የሚታይና የሚነበብ ሆኖ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ወይም ቢያንስ ከሁለቱ በአንዱ የተጻፈ መሆን አለበት፡፡

compliant measuring instrument; it shall ensure the withdrawal of such measuring instrument from further use or sale.

7/ For the purpose of inspection carried out pursuant to this Article, any measuring instrument found by the Inspector at the Premises of the user shall be considered to be used for business service.

## 13. Verification and Inspection of Pre-packaged Products

1/ No user shall export, import or distribute pre-packaged products without stating their net quantity, affixing the label thereof and without having a certificate of release issued by the Ministry.

2/ The label posted by the user on the pre-packaged products shall be conspicuously, legibly and unambiguously readable to customers that could not be easily removed and erased, which is printed in Amharic and English languages or at least one of them.

፫/በታሸጉ ምርቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም መግለጫ አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች መሰረት የሚዘጋጅ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን ዋና ዋና መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

ሀ) የምርቱ ስም፣ መለያ ቁጥር እና በእሽጉ ውስ ያለው የምርት ዓይነት፤

ለ)የተመረተበት ዓመተ ምህረት፤ወርና ቀን፤

ሐ) የመጠቀሚያ ማብቂያ ጊዜ፤

መ) የአምራቹ፣ የአሻጊው፣የላኪው ወይም የአስመጭው ስምና ምርቱ የተመረተበት ቦታ፤ እና

ሠ) የተጣራ የምርት መጠን፡፡

፬/ማንኛውም ተጠቃሚ የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን እና መግለጫ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለኢንስፔክተር ወይም ለሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፭/ማንኛውም ተጠቃሚ ለታሸገ ምርት ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና ምርመራ የሚሆን ወካይ ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ በገበያ ዋጋ ማቅረብ ይኖርበታል፤ የሚወሰደው ወካይ ናሙና በኢትዮጵያ ደረጃዎች መሰረት ይሆናል፡፡

3/ Any label posted on the pre-packaged products shall be prepared in accordance with the relevant requirements of Ethiopian standards and must bear at least the following main particulars:

a) Identity, common or generic name, code number and type of the product contained in the package;

b) Year ,month and day of manufacturing;

c) Expiry date;

d) Name and place of business of the manufacturer, packer, Exporter or Importer; and

e) The net quantity of the product.

4/ Any User shall submit pre-packaged products to the inspector or the legal metrology officer for the verification of the net quantity and label of same.

5/ Any User shall provide with market price, when required, a representative sample for the verification and inspection of pre-packaged products; The representative sample that will be taken shall be as per the requirements of Ethiopian standards.

፮/ሚኒስቴሩ የታሸገው ምርት የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው ወደ ውጪ ሀገር እንዲላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ለገበያ እንዲቀርብ ለተጠቃሚው የይለፍ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፯/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በማንኛውም ተጠቃሚ የግብይት ስፍራ በመግባት መደበኛ፣ ድንገተኛ ወይም የቀረበ ቅሬታን መሠረት በማድረግ የታሸገ ምርትምርመራ ማድረግ ይችላል፡፡

፰/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ምርመራ በሚያካሂድበት ጊዜ የታሸገ ምርት የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟላ ወይም ሕገወጥ መሆኑን ካረጋገጠ በዚህ አዋጅ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## ክፍል አራት

## የሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰሮች፣ ጠጋኞች እና ኢንስፔክተሮች ተግባርና ኃላፊነት

### ፲፬. የህጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር እና ጠጋኝ ተግባርና ኃላፊነት

፩/ማንኛውም የህጋዊ ስነ-ልክ ኦፊሰር በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል በተሰጠው ፈቃድ መሰረት በመንግሥት የሥራ ሰዓት በማንኛውም የግብይት ስፍራ

6/ The Ministry shall issue a certificate of release to the User allowing the export, import or sale of pre-packaged products if such products comply with the requirements of Ethiopian standards.

7/ The Ministry or the Relevant Body may undertake regular, surprise or complaint based visit at the premises of the User for the purpose of inspecting pre-packaged products.

8/ The Ministry or the Relevant Body may take administrative measures in accordance with this Proclamation when it ascertains that the pre-packaged products are illegal or do not comply to the relevant Ethiopian standards.

## PART FOUR

## POWERS AND DUTIES OF LEGAL METROLOGY OFFICERS, REPAIRERS AND INSPECTORS

### 14. Powers and Duties of Legal Metrology Officers and Repairers

1/ Any Legal Metrology Officer shall, in accordance with the license granted to him by the Ministry, enter any premises during government working hours and verify the accuracy of measuring instruments or

በመግባት የመለኪያ መሣሪያን ወይም የታሸገ ምርትን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤ የፈቃድ አሰጣጡ እና ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ማንኛውም ጠጋኝ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል በተሰጠው ፈቃድ መሰረት የመለኪያ መሣሪያ የጥገና ተግባራትን ያከናውናል፤ የፈቃድ አሰጣጡ እና ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ማንኛውም ሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር እና ጠጋኝ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል የተሰጠውን ፈቃድ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

፲፭.የኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት

ማንኛውም ኢንስፔክተር፡-

፩/ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል የተሰጠውን ደብዳቤ እና ኢንስፔክተር መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት ያለ ምንም ቅድመ ማስታወቂያ በማንኛውም የመንግሥት የሥራ ሰዓት ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት የሥራ ሰዓት

prepackaged products;

2/ Any repairer performs maintenance activities of measuring equipment according to the license given by the Ministry or the Relevant Body; The licensing requirements and his particular duties and responsibilities shall be determined by a directive.

3/ Any Legal Metrology Ofiicer and repairer shall carry out maintenance activities of measuring instruments in accordance with the license granted by the Ministry or Relevant Body; the licensing requirements and his particular duties and responsibilities shall be determined by directive issued here under.

15. Duties and Responsibilities of the Inspector

Any Inspector shall:

1/ Enter any premises, without advance notice during any regular working hours, or in doubtful cases out of the regular working hours, by showing his identification card and authorization letter issued by the Ministry or the Relevant Body, and inspect any measuring instruments and pre-packaged products as well as records

ውጭ፣ በማንኛውም የግብይት ስፍራ በመግባት የመለኪያ መሳሪያን ወይም የታሸገ ምርቶትን ትክክለኛነት እንዲሁም እነዚህን መሳሪያዎችና ምርቶች ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም መጠቀም አስመልክቶ ማናቸውንም መዛግብት መመርመር አለበት፡፡

regarding the manufacturing,assembling, exporting,importing, selling or use of such measuring instruments and prepackaged products.

፪/የመለኪያ መሣሪያው በኢትዮጵያ ደረጃዎች የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት በማድረግ ተጠቃሚው ከሚኒስቴሩ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

2/ Affix a verification mark and cause the issuance of a certificate of verification to the User from the Ministry if he finds that the measuring instrument complies with the requirements of Ethiopian standards.

፫/ የመለኪያ መሣሪያው የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟላ ሆኖ ካገኘው አገልግሎት ላይ እንዳይውል የሚያደርግ ምልክት ያደርግበታል፤ ይህንኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3/ Obliterate the stamp of verification and affix unusable mark and reject the verification certificate to the User if he finds that the measuring instrument does not comply with the requirements of Ethiopian standards and reports same to the Ministry or the Relevant Body.

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት የህጋዊ ስነ ልክ ኦፊሰር የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት ያደረገበት የመለኪያ መሳሪያ የተሳሳተ፣ የተበላሸ ወይም ትክክል ያልሆነ ሆኖ ካገኘው በመለኪያ መሳሪያው ላይ የተለጠፈውን የማረጋገጫ ምልክት

4/ Suspend the use of the measuring instrument, which the legal metrology officer verified and made verification mark up on it pursuant to Article 14 (1) of this Proclamation by rejecting the verification mark affixed on it when he proves that it is inaccurate, false or damaged and report this to the Ministry or the Relevant Body.

ውድቅ በማድረግ አገልግሎት እንዳይሰጥ ያደርጋል፤ ይህንኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

፭/የታሸገው ምርት በኢትዮጵያ ደረጃዎች የተደነገጉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሆኖ ካገኘው ተጠቃሚው ከሚኒስቴሩ የይለፍ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

፮/የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ያላሟላ የመለኪያ መሣሪያ ወይም የታሸገ ምርት ይዞ የተገኘ ማንኛውም ተጠቃሚ እንዳይጠቀምበት፣ እንዳይሸጠው፣ ከገበያ እንዲሰበስበው ወይም እንዲያስወግደው ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ያስፈጽማል፡፡

፯/ከተጠቃሚው የግብይት ስፍራ ማንኛውንም ነገር ለምርመራ የሚወስድ ከሆነ በመረካከቢያ ቅጽ ይረከባል፤ ምርመራውን ሲጨርስ ይመልሳል፡፡

፰/በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለአስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ስለቅጣት

5/ Cause the issuance of a certificate of release to the User from the Ministry if he finds that the pre-packaged product complies with the requirements of Ethiopian standards.

6/ Submit recommendation to the Ministry or the Relevant Body where he finds that any user possesses a measuring instrument or pre-packaged product, which does not meet the requirements of Ethiopian standards, to withdraw, collect or dispose or not to use or sell such measuring instrument or pre-packaged product and execute it when approved.

7/ Issue a receiving form to the user when he takes anything from the premises being inspected and return it after he has accomplished the inspection.

8/ Perform other related activities in accordance with the particulars specified by directives issued hereunder.

## PART FIVE

## ADMINSTRATIVE MEASURES AND PENALTY

## ፲፮.ክልከላዎች

አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

፩/የአንድን የመለኪያ መሣሪያ ወይም የመሳሪያውን ክፍል ዓይነት ወይም ንድፍ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ሳያጸድቅ እና የተስማሚነት የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ውጪ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፤

፪/በሚኒስቴሩ የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የመለኪያ መሳሪያን ማምረት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፤

፫/ተገቢውን መግለጫ ሳያደርግ፣ የተጣራ መጠን በመግለጫው ላይ ሳይገልጽ፣ ከመግለጫው ጋር በማይጣጣም ሁኔታ ወይም ከሚኒስቴሩ የይለፍ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የታሸገ ምርትን ማምረት፣ ማሸግ፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ፤

## 16. Prohibited Acts

Without prejudice to the provisions of other appropriate laws, committing the following acts is prohibited:

1/Manufacturing, assembling, exporting, importing or selling any measuring instrument or part thereof without type or design approval certificate of suitability by the Ministry;

2/ Manufacturing, exporting, importing or selling measuring instruments without a verification certificate issued by the Ministry;

3/Manufacturing, exporting, importing or selling any pre-packaged products without the required label, without describing the net quantity on the label, , inconsistent with the label or without having a certificate of release issued by the Ministry;

፬/የኢትዮጵያ የደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይመረት ወይም ለገበያ እንዳይቀርብ የተከለከለ የመለኪያ መሣሪያን ወይም የታሸገ ምርትን ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ለሽያጭ ማቅረብ፣ አገልግሎት ላይ ማዋል ወይም መጠቀም፤

፭/በመለኪያ መሣሪያው ላይ የተሳሳተ ወይም ተመሳስሎ የተሰራ ምልክት መጠቀም፤

፮/በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ ወይም በትክክል በማይሰራ የመለኪያ መሣሪያ አገልግሎት መስጠት ወይም መጠቀም፤

፯/ትክክለኛነቱ በተረጋገጠ የመለኪያ መሣሪያ ላይ የተደረገውን ምልክት በሌላ ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ የመለኪያ መሣሪያ ላይ መጠቀም፤

፰/ በመለኪያ መሳሪያ ላይ የተደረገውን ምልክት ወይም ማሸጊያ ማስወገድ ወይም የተወገደውን ምልክት መልሶ ማድረግ፤

፱/ በመለኪያ መሣሪያው ላይ ወይም መያዥያ ላይ ልኬቱን የሚለውጥ ተገቢ ያልሆነ ባዕድ አካል ማድረግ ፣

4/Manufacturing, assembling, exporting, Importing, selling, providing service or using any measuring instruments or pre-packaged products that do not conform to the requirements of Ethiopian standards or whose production or sale is prohibited in Ethiopia;

5/ Using a wrong or forged verification mark on the measuring instrument;

6/Providing service using improper measuring instrument or measuring instrument whose accuracy is not verified in accordance with this Proclamation;

7/Using a verification mark affixed on the measuring instrument whose accuracy is verified onother measuring instrument whose accuracy is not verified;

8/Detaching a verification mark or seal; or affixing a removed verification mark on the measuring instrument;

9/Affixing or putting an improper foreign matter on a measuring instrument or its container that can change its

መቀጠል ወይም የመሳሪያውን የአካል ክፍል መቀነስ፤

፲/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚደረግ ቁጥጥር አስፈላጊውን ትብብር አለማድረግ፣ ማደናቀፍ ወይም እንቢተኛ መሆን፤

፲፩/የመለኪያ መሳሪያውን በቀላሉ ልኬቱን ወይም የመለኪያ ውጤቱን ሊያዛባ ለሚችል የማጭበርበር ድርጊት በማይጋለጥበት ሁኔታ አለመጠበቅ፤

፲፪/ የህጋዊ ስነ-ልክ ኦፊሰር ወይም ጠጋኝ ሆኖ በመለኪያ መሳሪያ ወይም የታሸገ ምርት ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ ወይም መጠገን ስራ ላይ መሰማራት፡፡

፲፯.<u>አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ</u>

፩/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በሥልጣን ክልሉ ውስጥ የሚወድቁ የተከለከሉ ድርጊቶች ከተፈጸሙ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፡-

ሀ)በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) ከተመለከቱት የተከለከሉ ድርጊቶች አንዱ የተፈጸመ መሆኑን ሲያረጋግጥ

measurement;

10/ Impeding or obstructing in any way the work of inspection undertaken in accordance with this Proclamation;

11/Failure to maintain the measuring instrument in such a way that it is not susceptible to tampering that could easily distort the measurement or measurement result.

12/Engaging in the manufacturing, assembling, exporting, importing, selling or repairing of measuring instruments or pre-packaged products while being a Legal Metrology officer or a repairer.

17.<u>Administrative Measures</u>

1/ The Ministry or the Relevant Body may take one or more of the following administrative measures when prohibited acts falling within its jurisdiction are committed:

a) Bar measuring instruments or pre-packaged products from entering or leaving the country,dispose them or re-export them to the country of origin at the expense of the User, suspend their

እንደነገሩ አግባብነት የመለኪያ መሳሪያ ወይም የታሸገ ምርትወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ፣ ከሀገር እንዳይወጡ፣ በተጠቃሚው ወጪ እንዲወገዱ ወይም ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ፣ ስርጭታቸው እንዲቋረጥ፣ ከገበያ እንዲሰበሰቡ ወይም እንዲወረሱ ሊያደርግ ይችላል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከንዑስ አንቀጽ (፮) እስከ (፲) ከተመለከቱት የተከለከሉ ድርጊቶች አንዱ የተፈጸመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ተጠቃሚው አስፈላጊውን ማስተካከያ እስኪያደርግ ድረስ የሰጠውን የዓይነት ወይም የንድፍ ተስማሚነት የምስክር ወረቀት ወይም የትክክለኛነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ለተወሰነው ጊዜ ያግዳል፤ ተጠቃሚው በዕግዱ ጊዜ ተገቢውን ማስተካከያ ካላደረገ የምስክር ወረቀቱን በመሠረዝ የመለኪያ መሳሪያ እንዲወረሱ ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤

ሐ)በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) የተመለከተው የተከለከለ ድርጊት የተፈጸመ መሆኑን

distribution, recall them from market or decide their confiscation when it confirms upon credible evidence where one or more of the prohibited acts specified under Sub Article 1-5 of Article 16 of this Proclamation are committed;

b) Suspend the type or design approval certificate of suitability or any verification certificate of the User for the period specified by directives issued hereunder when it confirms upon credible evidence that one or more of the prohibited acts specified under Sub Article 6-10 of Article 16 of this Proclamation are committed and revoke such certificate and cause the confiscation or disposal of he measuring instrument if the User failed to make the necessary adjustment within the period of the suspension;

c) Revoke the license of a legal metrology officer or a repairer when it confirms upon credible evidence that the prohibited acts specified under

ሲያረጋግጥ ለሕጋዊ ሥነ-ልክ ኦፊሰር ወይም ጠጋኝ የሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፡፡

፪/ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወሰዳቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ህዝብ እንዲያውቃቸው ያደርጋል፡፡

፲፰.ቅሬታ ስለማቅረብ

፩/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደነገሩ አግባብነት ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታ በቀረበ በአስራአምስት የሥራ ቀናት ውሥጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው በ፴

Article 16 (11) of this Proclamation are committed.

2/ The Ministry or the Relevant Body shall notify to the public administrative measures taken in accordance with sub-article (1) of this Article.

18 Grievance

1/ Any person who is aggrieved with the decision of any concerned official regarding matters covered in this Proclamation, regulations and directives issued hereunder may lodge his complaint in writing to the Head of the Ministry or the Relevant Body, as appropriate, within ten working days from the rendering of such decision.

2/ The head of the Ministry or the relevant body shall notify his decision in writing to the aggrieved person within fifteen working days from the receipt of the complaint.

3/ The complainant may lodge his complaint to the competent Court within 30 days from the rendering of the decision if he is aggrieved by the decision of the Head of the Ministry or the Relevant Body or if he has not received a written decision within

ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፱.ስለቅጣት

፩/ማንኛውም ሰው ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለራሱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ከተመለከቱት የመለኪያ አሀዶች እና የአሃዶች ብዜቶች ውጭ በመጠቀም ምርት ወይም አገልግሎት ሲሸጥ ከተገኘ ከብር አስር ሺህ እስከ ሃምሳ ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፤ ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈጽሞ ከተገኘ ከብር ሃምሳ አንድ ሺ እስከ መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል፡፡

፪/ማንኛውም ሰው እያወቀ የመለኪያ መሣሪያዎችን ዓይነት ወይም ንድፍ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ሳያስጸድቅ እና የተስማሚነት የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው ሲያመርት፣ ወደ ውጭ ሀገር ሲልክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ ወይም ሲያከፋፍል ከተገኘ ከብር መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ማንኛውም ሰው ሌላውን ለመጉዳት ወይም

the time limit specified under sub-article (2) of this Article.

19. Penalty

1/ Whoever with intent to injure the interest of another, or to obtain undue advantage for himself sells a product or service using measuring units and multiples of measuring units other than referred in Article 5 of this Proclamation shall be punished with fine from Birr ten thousand to fifty thousand or with simple imprisonment not exceeding three years; when the prohibited act is committed for the second time, it shall be punishable with fine from Birr fifty one thousand to one hundred thousand or with simple imprisonment from six months to three years.

2/ Whoever knowingly engages in the manufacturing, exporting, importing or distributing of any measuring instrument without having type or design approval and a certificate of suitability shall be punished with fine from Birr one hundred thousand to two hundred fifty thousand or with simple imprisonment from six months to three years.

3/ Whoever with intent to injure the interest of

ለራሱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በዚህ አዋጅ መሠረት የመለኪያ መሳሪያን ለትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳያቀርብ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ ከብር አስር ሺ እስከ ሀያ ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

፬/ማንኛውም ሰው በሕግ ሥልጣን ሳይኖረው አስቦ የመለኪያ መሳሪያን የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት ካላቀቀ፣ በሌላ ከተካ ወይም የፕሎምብ እሽግን ከበጠሰ ከብር አንድ መቶ ሀምሳ ሺ እስከ ሦሥት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፭/ማንኛውም ሰው ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ተገቢውን መግለጫ ሳያደርግ፣ በመግለጫው ላይ የተጣራ መጠን ሳይገልጽ፣ በመግለጫው ላይ ከተገለጸው ጋር በማይጣጣም ሁኔታ ወይም የይለፍ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የታሸገ ምርት ሲያመርት፣ ሲያሽግ፣ ወደ ውጭ ሀገር ሲልክ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ፣ ለሽያጭ ሲያቀርብ ወይም በሌላ መንገድ ሲያስተላልፍ ከተገኘ ከብር መቶ ሺ እስከ ሁለት መቶ ሺ በሚደርስ መቀጮ እና ከሦስት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

፮/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)

another, or to obtain un due advantage for himself uses measuring instruments without submitting for verification in accordance with this Proclamation shall be punished with fine from Birr ten thousand to twenty thousand or with simple imprisonment not exceeding three years.

4/ Whoever with intent and without lawful authority detaches a verification mark, replaces it by another or tearing plumb seal of measuring instruments shall be punished with fine from Birr one hundred fifty thousand to three thousand and with rigorous imprisonment not exceeding five years.

5/ Whoever with intent to obtain un due advantage for himself manufactures, packs, exports, imports, sells or otherwise transfers any pre-packaged products without stating the net quantity on the label, containing less than the net quantity stated on the label, inconsistent with the label or without having a certificate of release shall be punished with fine from Birr one hundred thousand to two hundred thousand and with rigorous imprisonment not exceeding five years.

6/ Where the violation specified under sub-

ወይም (፫) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ከብር አስር ሺ. እስከ ሀያ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

፯/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ወይም (፭) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኛነት በሆነ ጊዜ ከብር ሀምሳ ሺ. እስከ አንድ መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

፰/ማንኛውም የሕጋዊ ስነ-ልክ ኦፊሰር ወይም ጠጋኝ ለራሱ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የመለኪያ መሳሪያን ወይም የታሸገ ምርትን ትክክለኛነት በዛባ ሁኔታ ካረጋገጠ ወይም ከጠገነ ከብር ፶ሺ. (ሀምሳ ሺ.ህ) እስከ ፩፻ሺ.(አንድ መቶ ሺ.ህ) በሚደርስ መቆጮ እና ከሶስት አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት ለማንኛውም የመለኪያ መሳሪያ የተሰጠ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ምልክት እና የምስክር ወረቀት በዚህ አዋጅ መሠረት

article (1), (2) or (3) of this Article is committed negligently, the punishment shall be fine from Birr ten thousand to twenty thousand or simple imprisonment not exceeding six months.

7/ Where the violation specified under sub-article (4) or (5) of this Article is committed negligently, the punishment shall be fine from Birr fifty thousand to one hundred thousand or simple imprisonment not exceeding one year.

8/ Any legal Metrology Officer or Repairer who checks or repairs the accuracy of measuring instruments or packaged products with the intention of obtaining undue benefit for himself or for another person, shall be fined between 50,000 (fifty thousand) and 100,000 (one hundred thousand) and is punishablet for a term not exceeding three years simple imprisonment.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 20. Transitory Provisions

1/ Any verification mark and certificate of verification granted to any measuring instruments prior to the effectiveness of this Proclamation shall remain in force until

እስኪተካ ድረስ እንደጸና ይቆያል፡፡

፪/ በሚዛንና መስፈሪያ ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፬፻፴፩/፩ሺ፱፻፷፭ የተወሰነው የአገልግሎት ክፍያ በሌላ የአገልግሎት ክፍያ ደንብ እስኪተካ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

<u>፳፩.ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ የመለኪያ መሳሪያዎች ድጅታል በሆኑ የመለኪያ መሳሪያዎች ይተካሉ። አገልግሎት ላይ የሚውልበት ጊዜ ዝርዝር አሰራር በመመሪያ ይወሰናል።

<u>፳፪.የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/የሚዛንና መስፈሪያ ደንብ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፬፻፴፩/፩ሺ፱፻፷፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

replaced in accordance with this Proclamation.

2/ The Service Fee determined by Weights and Measures Regulation legal notice No. 431/1973 shall remain in force until it is replaced by another service fee regulation.

21. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article 1 of this Article.

3/ The measuring instrument shall be replaced by a digital measuring instrument. The detailed procedure for the period of service shall be determined by a directive.

22<u>. Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ Weights and Measures Regulation legal notice No. 431/1973, is hereby repealed.

2/ No Proclamation, Regulation, Directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters covered by this Proclamation.

፳፫.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

23. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this 10th day of September 2024

SAHILEWORK ZEWDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA